የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የኢሚግሬሽን ዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ
# 2011 በጀት ዓመት ሂሣብ
# ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት /2012

አዲስ አበባ

# የኢሚግሬሽን ዜግነትና የወሳኝኩነት ኤጀንሲ

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የኢሚግሬሽን ዜግነትና የወሳኝኩነት ኤጀንሲ የተመደበለትን መደበኛ በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የኤጀንሲው የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**የጥሬ ገንዘብ፤**

1. ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ ከብር 5,000.00 በላይ ከሳጥን ወጪ ሆኖ በድምሩ ብር 15,786.34 ተገኝቷል፡፡

**የገቢ ሂሳብ፤**

2. በዕለቱ ባንክ ገቢ ያልተደረገ ከኢምግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ብር 1,835,398.80 እንዲሁም ከኢሚግሬሽን ዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ብር 376,391.28 በጠቅላላ በድምሩ ብር 2,211,790.08 ተገኝቷል፡፡
3. ከኢሚግሬሽን ዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ብር 30,067,332.14 እንዲሁም በኢሚግሬሽን ዋና መምሪያ ብር 79,175,045.36 በድምሩ ብር 109,242,377.50 በተለያዩ የገቢ ደረሰኞች የተሰበሰበ ገቢ በሞዴል 64 ሳይጠቃለል ተገኝቷል፡፡
4. ከኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ተቀናሽ ያልተደረገ የህክምና መዋጮ ብር 1,474.20 ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

**የወጪ ሂሳብ፤**

5. አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ድርጅት እያለ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት ግዥ በመፈጸሙ ብር 292,600.00 በብልጫ ወጪ በመደረጉ መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ ተዳርጓል፡፡
6. በድምሩ ብር 78,146.30 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች ተገኝተዋል፡፡
7. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይኖር ለውሎ አበል ተብሎ በድምሩ ብር 34,210.41 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
8. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይኖር ለተለያዩ አገልግሎቶች በድምሩ ብር 90,209.25 ክፍያ ተፈጽሞ ተገገኝቷል፡፡
9. ኤጀንሲው ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በውስን ጨረታ በብር 361,068.29 የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ለተሰጠበት ለኢትዮ ሪዞርት ኃ/የተ/የግ/ማ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

10. ጨረታ ሳይወጣ እና አቅራቢዎች ሳይወዳደሩ በቀጥታ የኪራይ አገልግሎት ግዥ ለተፈፀመበት ብር 2,010,791.08 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

11. አለአግባብ የውሎ አበል ብር 14,544.00 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

12. በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2(ሠ) ለዋና ዳይሬክተር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት እንዲሁም በደብዳቤ ቁጥር ብመደአ1/8964 ጥር 10 ቀን 2009 ዓ.ም በተገለጸው መሠረት ለኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ለ2011 በጀት ዓመት ለስምንት ወራት ወጪ ከተደለደለው በጀት ብር 164,759,258.67 ውስጥ ብር 71,079,531.86 ሚስጥር በመሆኑ በመ/ቤታችን ኦዲት አልተደረገም ፡፡

**ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

13. በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 25,369,906.07 ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 13 በተገለፁት ሁኔታዎች መሠረታዊነትና ጉልህነት የተነሳ የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች ፤**

14. ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 7,061.55 ተገኝቷል፡፡

15. በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ሠራተኛ/ኃላፊ ሳይረጋገጥ በድምሩ ብር 3,016,488.80 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

16. በሥራ ላይ ያልዋለ ከመደበኛ በጀት ብር 149,939,452.10 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 9,327,508.88 (98.52) ተገኝቷል፡፡

**ሌሎች ጉዳዮች፤**

17. **የንብረት አስተዳደርን በተመለከተ፤**

**በቀድሞ የፌዴራል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ**

- በየዓመቱ የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ የማይደረግና ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፡፡

- በቋሚ ንብረት መጋዘን የተለያዩ ወንበሮች ፤ላፕቶፕ ስልክ ሃርድ ዲስክ የሚወገዱ እና አገልግሎት የሚሰጡ እቃዎች ተለይተው ያልተቀመጡ መሆናቸውን፤ አመቺ ባልሆነ ሁኔታ እንዲቀመጡ መደረጉና የሚወገዱ እቃዎች እንዲወገዱ አለመደረጉ፡፡
- የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) የሚያዘጋጅና የንብረቶች ዕቃ ግምጃ ቤት የመቆጣጠር ኃላፊነት በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑን፤

<u>**የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ**</u>

መምሪያው የሚገለገልባቸው ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሮች ለኦዲቱ ያልቀረቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>**በኢሚግሬሽን ዜግነትና የወሳኝኩነት ኤጀንሲ**</u>

- በአላቂ የንብረት መጋዘን ውስጥ 6 ሱፍ የሴት የደንብ ልብስ ከ ሶስት አመት በላይ ፡ተቀምጠው የተገኘ እና በተጨማሪም ባለቤቱ የማይታወቅና ሞዴል 19 ሳይቆረጥ በአደራ የተቀመጠ ፤
- በቋሚ ክፍል ውሰጥ ደግሞ ፓስፖርት ሊሴፓሴ ላምኔት የተለያዩ የህትመት ውጤቶች ከቋሚ ንብረት ጋር ተደባልቀው ተገኝተዋል፤
- የተለያዩ ወንበሮች ፤ጠረጴዛዎች፤ ፎቶ ኮፒ፤ ሼልፎች፤ ኮምፒዩተር እንዲሁም በባለሞያ ያልተፈተሹ ሊወገዱ የሚገባቸውና እንዲወገዱም ምንም ጥረት ያልተደረገላቸው የብዙ ዘመናት ፓስፖርት እና አገልግሎት የሚሰጡ አዳዲስ ጠረጴዛዎች ፣ ድሮወር ፣ ሰርቨር፣ የኮምፒተር መለዋወጫ ፣ አዳዲስ ሞተር ሳይክል፣ መጋረጃና ወንበር ለቁጥጥር በማያመች መልኩ ተደራርበው በኤጀንሲው ቢሮ ኮሪደር አካባቢ እና በየሽንት ቤት ውስጥ ተከማችተው እና በሜዳ ላይ ፀጸሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው መገኘቱ፡፡
- የፓስፖርት ስቲከር ህትመቶች ወደ ንብረት ክፍል ደርሰው በሞዴል 19(ንብረት ገቢ) ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ እና አየር በአየር በንብረት ክፍል የወጪ ደረሰኝ በሞዴል 22 ወጪ እንደሆኑ ታውቋል፡፡

**<u>ሌሎች ጉዳዮች</u>**

18. የሰነድ ያዥ ቢሮ እና የገንዘብ ያዥ ቢሮ በአንድ ክፍል ውስጥ ሁለቱም የስራ ክፍል እየሰራ መገኘቱ፤
19. ኤጀንሲው የበጀት ዓመቱን የግዥ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ፤
20. ከሽ.ዛ ሂሳብ ገቢ የሆኑት የሽ.ዛ ስቲከር ቁጥሮች በተለያየ የገቢ ደረሰኝ ላይ ተደጋግሞ መገኘትና በቅደም ተከተል መሰረት የማይመዘገብ መሆኑ፤
21. በአቃፊ /Box File/ ላይ ያለው የገቢም ሆነ የወጪ ማስመስከሪያ በቀደም ተከተል ያለማስቀመጥ እና የተሟላ ምዝገባ ያለማድረግ፤
22. ኤጀንሲው ከመደበኛ ፓስፖርት ውጪ የተገኘ ገቢ ማለትም ከጠፋ ፓስፖርት እንዲሁም አስቸኳይ ፓስፖርት ገቢ የተሰበሰበው የገቢ ደረሰኝ ቁጥር የማይጠቃቀስ መሆኑ፤

ከሰላምታ ጋር

-------------

ትዕግስት ረታ
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር